# <u>የሚጓዙ እንስሳት</u>

የተለያዩ እንስሳቶች በአለማችን ላይ ሲገኙ እያንዳንዳቸው የተለያየ ባህሪይ አላቸው፡፡ አንዳንድ እንስሳቶች ከአንደኛው የአለማችን ጫፍ እስከ ሌለኛው ይጓዛሉ፡፡ አካላቸው ትንሽ ቢሆንም አቅጣጫቸውን ሳይስቱ ረጅም ጉዞዎችን ማድረግ ይችላሉ፡፡ አሁን ከእነዚህ ፍጥረታቶች መካከል አንዱ ስለሆነው የሞናርክ ቢራቢሮ እንመልከት፡፡

## የሞናርክ ቢራቢሮ ጉዞ

የሞናርክ ቢራቢሮ በደቡባዊ ካናዳ ይኖራል፡፡

እንደሌሎች ቢራቢሮዎች ሁሉ ሞናርክ ከመወለዱ በፊት ተከታታይ ለውጦችን ያካሂዳል፡፡ መጀመሪያ እናት ሞናርክ እንቁላሏን በቅጠል ላይ ትጥላለች፡፡ ከእንቁላሉ የሚፈለፈለው እጭ ለጥቂት ጊዜያት ቅጠሉን ይመገባል፡፡ በመቀጠል ወደ አባጨጓሬነት ይቀየራል፡፡ ከዚያም ኩኩን በመባል የሚታወቅ የተቆለፈ ጎጆ ይሠራል፡፡

የሞናርኩ ኩኩን ከዛፍ ጋር ቀጭን ሆኖም ጠንካራ በሆነ መገናኛ ተያይዟል፡፡ ሽፋኑ ውስጥ የሚገኘው አባጨጓሬ ቀስ በቀስ ብቅ ማለት ይጀምራል፡፡ መጀመሪያ ላይ ክንፎቹ የተነፈሱ ናቸው፡፡ ነገር ግን ደም ወደነሱ መነፋት ሲጀምር ይሞላሉ፡፡ አሁን ሞናርኩ ለመብረር ዝግጁ ነው፡፡

ሞናርኮች ከሌሎች ቢራቢሮዎች የሚለያቸው ልዩ የሆነ ባህሪይ አላቸው፡፡ በአንድ ዓመት ውስጥ አራት የተለያዩ የሞናርክ ትውልዶች ይኖራሉ፡፡ የመጀመሪያዎቹ ሶስቱ አማካኝ እድሜያቸው ከአምስት እስከ ስድስት ሳምንታት ነው፡፡ ነገር ግን አራተኛው ትውልድ ይለያል፡፡ ይህ ትውልድ ስምንት ሳምንታት የሚፈጀውን ጉዞ ያደርጋል፡፡ ጉዞውንም ለመሸፈን ለስምንት ሳምንታት ይቆያል፡፡

ጉዞው የሚጀምረው ደቡባዊ ካናዳ ውስጥ ከሚገኙ የተለያዩ የሞናርክ ቢራቢሮ ማዕከላት ሲሆን የጉዞው አቅጣጫም ወደ ደቡብ ነው፡፡ አንዱ ቡድን ወደ ካሊፎርኒያ ሲጓዝ ሌላኛው ደግሞ የበለጠ ወደ ደቡብ በመጓዝ ወደ ሜክሲኮ ያቀናል፡፡ እነዚህ የተያዩ የሞናርክ ቡድኖች

ከአንድ ማእከል ትእዛዝ የተሰጣቸው በሚመስል ሁኔታ መንገድ ላይ በመገናኘት ጉዞአቸውን አንድ ላይ ይቀጥላሉ፡፡

እነዚህ ቢራቢሮዎች ጉዞአቸውን የሚጀምሩት ቀኑና ሌሊቱ እኩል በሚሆኑበት የመኸር እለት ነው፡፡

ለሁለት ወራት ከበረሩ በኋላ ሞቃታማው ደቡባዊ ደን ይደርሳሉ፡፡ ዛፎቹ በሚሊዮን በሚቆጠሩ ሞናርኮች ተሞልተዋል፡፡ ሞናርኮች እዚህ ከታህሳስ እስከ መጋቢት ይቆያሉ፡፡ በነዚህ አራት ወራት ውስጥ ምንም ነገር አይበሉም፡፡ አካላቸው ውስጥ የተጠራቀመውን ስብ እና ውሀ ብቻ በመጠጣት ይኖራሉ፡፡

በፀደይ ወቅት መፍካት የሚጀምሩት አበቦች ለሞናርኮች እጅግ ጠቃሚ ናቸው፡፡ አሁን ለአራት ወራት ያለምንም ምግብ ከጠበቁ በኋላ ከአበባ ማሩ ይቋደሳሉ፡፡ አሁን ወደ ሰሜን አምሪካ ለሚያደርጉት ጉዞ በቂ የሆነ ኃይልን አጠራቅመዋል፡፡ በመጋቢት ወር ጉዞአቸውን ከመጀመራቸው በፊት ግንኙነት ያደርጋሉ፡፡ የቀን እና የሌሊቱ እርዝመት እኩል በሚሆንበት እለት የሞናርኩ ቡድን ወደ ሰሜን መብረር ይጀምራል፡፡ ጉዞዋቸውን በመጨረስ የዝርያቸውን ቀጣይነት የሚያረጋግጠውን ትውልድ ይወልዳሉ፡፡

አዲሱ ትውልድ የአመቱ የሞናርክ ትውልድ መጀመሪያ ሲሆን ለአንድ ወር ከግማሽ አካባቢ ይኖራል፡፡ በመቀጠል  ሁለተኛው እና ሶስተኛው ትውልድ ይተካሉ……አራተኛው ትውልድ ሲተካ ጉዞውን በድጋሚ ይጀምረዋል፡፡ ከሌሎች በስድስት ወራት የረዘመ እድሜን ይኖራል፡፡ እናም ሰንሰለቱ በዚህ መልኩ ይቀጥላል…

አሁን ለአፍታ ያህል ስለዚህ አስደናቂ ጉዞ እናስብ፡፡

- እንዴት ነው ከአራቱ ትውልዶች አንዱ ከሌሎች በስድስት ወራት የበለጠ እድሜ ሊኖረው የቻለው ?
- ለምን ለረጅም ጊዜ የሚቆየው ትውልድ በበጋ ወራት ይሰበሰባል?
- እንዴት ነው ቢራቢሮዎች ጉዞዋቸውን የሌሊቱ እና የቀኑ እርዝመት እኩል ሲሆን የሚጀምሩት? እንዲሁም እንዴት ይህን ትክክለኛ ስሌት ማድረግ ቻሉ?

- አዲስ የተወለደው ቢራቢሮ ከዚህ በፊት አድርጎት የማያውቀውን የጉዞ መንገድ እንዴት ሊያውቅ ቻለ?

እነዚህ ሁሉ የሚያሳዩት የሞናርክ ቢራቢሮዎች እንከን በማይወጣለት ንድፍ ለስደት የተፈጠሩ እንደሆነ እና እያንዳንዱን የጉዞ ንድፍ በተገቢው መልኩ እንደሚወጡት ነው፡፡ ምናልባት በንድፉ ላይ የሰናፍጭ ታክል ስህተት ቢኖር የሞናርክ ቢራቢሮዎች በተገቢው መልኩ ጉዞአቸውን ባለፈፀሙ ነበር፡፡ በዚህም ሁኔታ የሞናርክ ቢራቢሮዎች በሙሉ በቀዝቃዛዎቹ የክረምት ወራት በመሞት ዝርያቸው ወደ መጥፋት ደረጃ ይደርስ ነበር፡፡

በርግጥ እነዚህ ፍጥረታቶች ይህን በየዓመቱ የሚያካሄዱትን ልዩ ጉዞ እንዲጨርሱ በልዩ ሁኔታ ተፈጥረው ተምረዋል፡፡ የዚህ አስደናቂ ጉዞ ፈጣሪ ሰማይ እና ምድርን ያስገኘው እንዲሁም የሁሉም ነገሮች ፈጣሪ እና ዳኛ የሆነው ሃያሉ አላህ ነው፡፡

## ይህን ያውቁ ኖሯል...?

## <u>ሸማኔ ወፎች</u>

ሸማኔ ወፎች ጎጆአቸውን ሳሮችን በመሸመን ይሠራሉ፡፡

ጎጆ ለመስራት ሸማኔው ወፍ መጀመሪያ ባለ ሦስት ጎን ጣራ ይሠራል፡፡ በኋላም ሦስት የተለያዩ አይነት ቋጠሮዎችን በመጠቀም ይህን ቦታ ይዘጋዋል፡፡

ሁሉም ጎጆ ጠንካራ ጣራ፣ ግንቦች እና መግቢያ አለው፡፡

መጀመሪያ ወፉ የሚሠራው ረጅም እና ቀጭን የሳር ጫፍን ከቀጭን ቅርንጫፍ ጋር ማገናኘት ነው፡፡

ነገር ግን ይህ ቀላል አይደለም፡፡ ይህን ነጠላ ቋጠሮ አንድ ቦታ ላይ ለማሠር ሸማኔው ወፍ ጠንክሮ መስራት አለበት፡፡

ይህ የመጀመሪያው ቋጠሮ በትክክል መሠራቱ በጣም ወሳኝ ነው፡፡

ያለዚያ ጎጆውን ለመስራት የሚያስችል መሠረት አይኖረውም፡፡

የመጀመሪያው ቋጠሮ በትክክል ካልተሠራ ቀጣይ ደረጃዎች በመጀመሪያው ቋጠሮ ላይ ስለሚመሠረቱ ይበላሻሉ፡፡

ቋጠሮዎቹ ይበዙ እና ክብ ነገር ይሰራል፡፡

ወፉ የሰራውን ክብ ነገር አቅጣጫዎች በትክክል ማስላት አለበት፡፡ ይህ ክብ ነገር ለሱ የሚያስገባው መሆን አለበት፡፡ ነገር ግን ከሱ የተለቁ ወፎችን ላለማስገባት ትንሽ መሆን አለበት፡፡ወፉ ይህንን ክብ በትክክለኛው መጠን በመስራት ሁልጊዜም ይሳካለታል፡፡

ዋናውን ክብ ሰርቶ ጎኖቹን ከዘጋ በኋላ ሸማኔው ወፍ ጣራውን መስራት ይጀምራል፡፡

ከላይ እስከታች ሳሮቹን ይደረድራቸዋል፡፡ ይህን ዘዴ በትእግስት በመተግበር ምሉእ የሆነ ጎጆን ይሠራል፡፡

ሸማኔ ወፎች የሚኖሩባቸውን ዛፎች ስንመለከት፡፡ አንድ ቤትን ሳይሆን በመቶዎች በሚቆጠሩ ቤቶች የተገነባ ግዙፍ ከተማን እንመለከታለን፡፡

ሁሉም ሸማኔ ወፍ አላህ ባሳወቀው መሠረት ተመሳሳይ ቤትን ይሠራል፡፡

## የሳልመን ስደት

ሳልመን በሰሜን አሜሪካ ምዕራባዊ ጫፍ በሚገኙ ወንዞች ስር ይኖራል፡፡

እናት ሳልመን እንቁላሎችዋን ወንዝ ውስጥ ጥልቀቱ ዝቅተኛ በሆነ ቦታ ላይ ትጥላለች፡፡ የሚፈለፈሉት ትናንሽ ሳልመኖች በእንቁላል ውስጥ ካለው የምግብ ከረጢት ይመገባሉ፡፡ ከጥቂት ሳምንታት በኋላ በወንዙ ስር ምግብ ማግኘት ይችላሉ፡፡ ወንዙ ውስጥም ለአንድ አመት አከባቢ ይቆያሉ፡፡

ሳልመኖች በንፁህ እና በጨዋማ ውሀ ውስጥ እንዲኖሩ ተደርገው ነው የተፈጠሩት፡፡ የዚህ አላማ አሳው በሚያደርገው ጉዞ ላይ ተደብቆ ይገኛል፡፡

በአንድ የፀደይ ቀን በሺዎች የሚቆጠሩ ሳልመኖች ከወንዙ መሰደድ ይጀምራሉ፡፡ ለሳምንታት ከፈጀው ጉዞአቸው በኋላ መድረሻ ቦታቸው ላይ ይደርሳሉ፡-የሰላማዊው ውቅያኖስ

ውቅያኖሱን እንደደረሱ በሳልመኑ አካል ላይ የሚካሄደው የይዘት ለውጥ አሳውን በጨዋማ ውሀ ውስጥ እንዲኖር ያስችለዋል፡፡ በቀጣዮቹ ከአንድ እስከ አራት ዓመታት ውስጥ በውቅያኖስ ላይ ብዙ ርቀትን ያቋርጣሉ፡፡ ከአሜሪካ ጫፍ በመነሳት የአላስካን የባህርዳርቻዎች ያልፋሉ፡፡ በትልቅ አርክወደ ጃፓን ይዋኙ እና እንደገና ይመለሳሉ፡፡ በጉዞው መጨረሻ ሳልመኖቹ የመጨረሻ እና በሕይወታቸው እጅግ አስቸጋሪ ለሆነው ሌላ ልዩ ጉዞ ተዘጋጅተዋል፡፡ ወደ ተወለዱበት ወንዝ ይመለሳሉ፡፡

ከአመታት በፊት ወደ ባህር ለመድረስ በዋኙበት ወንዝ ይዋኛሉ፡፡ ነገር ግን አሁን የሚዋኙት ከፍሠቱ ወደላይ በተቃራኒ አቅጣጫ ነው፡፡ ማንኛውም መሰናክል አያስቆማቸወም፡፡ ፏፏቴዎችን ለማቋረጥ በመዝለል ጉዞአቸውን ይቀጥላሉ፡፡ የሚገጥማቸውን መሰናክል እስከ ሶስት ሜትር ዝርመት በመዝለል ያልፉታል፡፡

አንዳንድ ጊዜ ሶስት ሺህ ሁለት መቶ ኪሎ ሜትሮችን ይጓዛሉ፡፡በዚህ ጉዞ በሙሉ ባህር ወስጥ እያሉ ያጠራቀሙትን ኃይል በመጠቀም ምንም አይመገቡም፡፡ በመጨረሻ ሳይጠፉ ከዓመታት በፊት የተለዱበት ወንዝ ዳርቻ በመድረስ እንቁላላቸውን ይጥላሉ፡፡ ኃላፊነታቸውን ተወጥተዋል፡፡

ይህ የሳልመን ስደት ከተፈጥሮ አስደናቂ ጉዞዎች እንዱ ነው፡፡ አመታትን በባህር ውስጥ ካሳለፉ በኋላ እንዴት በሺዎች የሚቆጠሩ ሳልመኖች የተለዱበትን ወንዝ ሊያገኙ ቻሉ? ይህን ለማድረግ ወደ ውቅያኖስ ውስጥ ከሚፈሱት በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ገባር ወንዞች የራሳቸውን ወንዝ ማግኘት አለባቸው፡፡ በመቀጠል በዚህ ወንዝ ሳይጠፉ መዋኘት እና በእያንዳንዱ ወንዙ በሚከፈልበት ስፍራ ትክክለኛ ውሣኔ መወሰን አለባቸው፡፡

ይህ ሲታይ የማይቻል የሚመስልን ስራ ሳልመኖች በአግባቡ ይወጡታል፡፡ጥሩ እንዴት ይህን ማድረግ ቻሉ ? ምክንያቱ ምንድን ነው?

ሳይንሳዊ ጥናቶች ሳልመኖች ጉዞአቸውን እንዲጨርሱ የሚያስችል በልዩ ሁኔታ የተፈጠረ የማሽተት ስርዓት እንዳላቸው አሳይተዋል፡፡ በባህር ውስጥ እያሉ አቅጣጫቸውን ለማግኘት የመሬትን ማግኔታዊ ዛቢያ ከሚለይ ኮምፖስ ጋር ነው የተፈጠሩት፡፡ ለዚህ ምስጋና ይግባው በሰላማዊው ውቅያኖስ ሳይጠፉ አቅጣጫቸውን ማግኘት ይችላሉ፡፡

ነገር ግን እጅግ ወሳኙ ጥያቄ እነዴት ሳልመኖች የተወለዱበትን የወንዝ ዳርቻ ማግኘት ቻሉ የሚለው ነው፡፡ለዚህ ከአቅጣጫ ጠቋሚ ኮምፓስ በተጨማሪ ሌላ የተለየ ስርዓት ያስፈልጋል፡፡

በዚህ ላይ የተደረጉ ጥናቶች ሳልመኖች የውልደት ቦታዎችን የሚያገኙት ሽታውን በመከተል እንደሆነ አሳይተዋል፡፡

ወንዞች የራሳቸው ሽታ ይኖራቸዋል ብለን ላናስብ እንችላለን፡፡ ሆኖም እየንዳንዱ በአለም ላይ የሚገኝ ወንዝ የራሱ የሆነ ኬሚካላዊ ውህድ አለው፡፡ በነዚህ ኬሚካላዊ ውህዶች መካከል ያለው ልዩነት እጅግ አነስተኛ በመሆኑ ከሳልመን በስተቀር በማንኛውም ፍጥረት መለየት አይችልም፡፡

ስለሳልመን ልዩ ታሪክ ለጥቂት ጊዜ እናስብ፡-

እያንዳንዱ የሳልመኑ የጉዞ ሂደት በጥንቃቄ እንደተሰላ ትረዳላችሁ፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ በሳልመኑ አካል ውስጥ ከአመታት በፊት ወደ ተወለደበት ወንዝ እንዲመለስ የሚያዘው ኘሮግራም መኖሩ ትልቅ ተዓምር ነው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በባህር ውስጥ ሳልመኑ አቅጣጫውን እንዲያገኝ የሚያደርገው ኮምፓስ እንዲሁም ይህ አሳ የአለማችን እጅግ የላቀ የማሽተት ስርአት መያዙ በድንገት ያልተገኙ ነገሮች ናቸው፡፡

እነዚህ ሁሉ ሳልመን ለታቀደለት ጉዞ በልዩ ሁኔታ መፈጠሩን ያመለክታሉ፡፡

ሳልመንን በነዚህ ልዩ ባህሪያት የፈጠረው የሁሉም ነገር ፈጣሪ እና የአለማት ጌታ አላህ ነው፡፡

በቁርአን አላህ (ሡ.ወ) የሱን የፈጠራ ጥበብ በሁሉም ሕይወት ያላቸው ነገሮች ማየት እንደምንችል ገልፆልናል፡፡

**“እናንተን መፍጠሩ ፤ ምድር ላይ እንሰሳትን መርጨቱም ፅኑ እምነት ላላቸው ሰዎች ተአምራት ናቸው፡፡” (ቁርአን 45:4)**

## ይህን ያውቁ ኖሯል.......?

## ሸክላ ሰሪ ንቦች

የምትመለከቷቸውን ትናንሽ ማሠሮዎች የሠራቸው ማን እንደሆነ ታውቃላችሁ? የንብ ዝርያ ነው ይህ ንብ ተጣባቂ ጭቃን ምራቁን ከረጠበ አፈር ጋር በመደባለቅ ይሠራል፡፡ ይህን ጭቃ በመጠቀም የሰው ልጅ በሸክላ ስራ የሚሰራውን አይነት ለስላሳ ማሠሮዎችን ይሠራል፡፡ ንቡ አፈሩን ባለማቋረጥ በማዞር ማሠሮዎችን ቅርፅ ያሲዛቸዋል፡፡ ማሰሮውን ሰርቶ ሲጨርስ የማሰሮውን አፍ ላዩ ላይ መስራቱን አይዘነጋም፡፡

ማሰሮው ተሰርቶ ሲያልቅ ንቡ ጀርባውን ወደ ማሠሮ አፍ በማዞር እንቁላሉን ይጥልበታል፡፡ የተወሰነ ምግብ ማሰሮው ውስጥ ካስቀመጠ በኋላ የማሠሮውን አፍ በማሸግ ይበራል፡፡ ከእንቁላሉ የሚፈለፈለው እጭ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ማሰሮውን በመስበር ወደ አዲሱ ሕይወቱ ይመጣል፡፡ እነዚህ በትናንሽ ንቦች ተሰብረው የተተዉ ማሠሮዎች ናቸው፡፡

ትናንሽ ንቦች ወደዚህች አለም ከመጡ በኋላ ያለምንም ልምምድ ልክ እንደ እናቶቻቸው ምሉእ የሆኑ ማሰሮዎችን መስራት ይጀምራሉ፡፡ ይህን አስደናቂ ጥበብ የሚያስተምራቸው አላህ ነው፡፡

## መደምደሚያ

በዚህ ፊልም ላይ የተመለከትናቸው ፍጥረታት አላህ (ሱ.ወ) የሠጣቸውን ፀጋዎች አሳይተውናል፡፡ እነዚህ ፍጥረታቶች በሙሉ በአላህ ፈጠራ ምክንያት ይሠራሉ፡፡

አላህ (ሱ.ወ) እኛን እና ሌሎች በአለም ላይ የሚገኙ ሕይወት ያላቸው ነገሮችን ፈጥሯል፡፡ ለእያንዳንዱ ፍጥረት የራሱ የሆነ የተለየ ባህሪይ በመስጠት አላህ (ሱ.ወ) ለሰው ልጆች የእሱን የመፍጠር ጥበብ ታላቅነት ያሳያል፡፡ የአላህን ኃይል እና ታላቅነት ለሌሎች

መንገር እና ማመስገን የእኛ ኃላፊት ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) ይህን እውነታ በቁርአን አማካኝነት ያሳውቀናል፡-

> “ምስጋና ለአላህ ይሁን፡፡ ለሰማያት እና ለምድር ኔታ፤ ለአለማት ጌታ፡፡ በሰማያትም በምድርም ውስጥ ክብር እና ልእልናም ለርሱ ይሁን፡፡ እርሱ ሀያል እና ጥበበኛ ነው፡፡” ቁርአን 45፡36-37